# የነዳጅ ውጤቶችን የግብይት ሥርዓት ለመደንገግ በተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅ ላይ የቀረበ አጭር መግለጫ

የነዳጅ ውጤቶች ካላቸዉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ አንጻር ስትራቴጂክ ምርቶች በመሆናቸዉ አቅርቦታቸውን፣ ክምችታቸውን፣ ስርጭታቸውን፣ ዋጋቸውን፣ ጥራታቸዉን እና ደህንነታቸውን መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣ የነዳጅ ውጤቶች ከአስመጪ ጀምሮ እስከ ተጠቃሚዎች ድረስ ያለው ግብይት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ፣ ግልጽ፣ ፍትሐዊ እና ተደራሽ የሆነ የአቅርቦት ሰንሰለት የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ለፈጻሚው እና ለአስፈጻሚው የተመቸ የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ በመሆኑ እና በነዳጅ ውጤቶች ግብይት ሥርዓት ውስጥ እየታዩ ያሉ የመደበቅ፣ ከባዕድ ነገር ጋር የመቀላቀል፣ አቅጣጫ የመቀየር፣ ሕገ-ወጥ የግብይት ሥርዓት፣ ኮንትሮባንድ እና የመሳሰሉ ችግሮችን በማስወገድ በመስኩ ሕጋዊ የግብይት ሥርዓት ማስፈን በማስፈለጉ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ማድረስ እንዲቻል ይህ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

ይህ ረቂቅ አዋጅ ሲዘጋጅ በነዳጅ ዘርፍ ያጋጠሙ ችግሮችን በመመርመር፣ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ተሞክሮዎችንና አሰራሮችን እንዲሁም የህግ ማዕቀፎችን በመፈተሽ ላጋጠሙ ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ የህግ ሃሳቦች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ረቂቅ አዋጁ አራት ክፍሎች እና 28 አንቀጾች ያሉት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

የረቂቅ አዋጁን አጭር ርዕስ፣ የቃላት ትርጓሜ እና የተፈጻሚነት ወሰን አካቶ ይዟል፡፡

በአንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው የአዋጁ አጭር ርዕስ “ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት አዋጅ” የሚል ሲሆን በትርጓሜ አንቀጽ 2 ደግሞ በአዋጁ ዉስጥ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸዉ 22 ቃላት ትርጉም እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 3 የተቀመጠው የተፈጻሚነት ወሰን አዋጁ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ የነዳጅ ውጤቶች የግብይት ሰንሰለት እና በግብይት ተዋናዮች ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ አዋጁ በመላው ኢትዮጵያ ተፈጻሚ እንዲሆን የተደረገው ሕጉ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 55 (4) መሠረት የንግድ ሕግ አካል በመሆኑ እና የነዳጅ ውጤቶች ተገዝተው ወደ ሀገር ውስጥ

የሚገቡትና በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች  የሚሰራጨት የፌዴራሉ መንግሥት በሚመድበው የውጪ ምንዛሪ በመሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩል አዋጁ ራሱን በቻለው የማእድን ፍለጋና ልማት ሕግ በሚተዳደረው በላይኛው የማዕድን ንዑስ ኢንዱስትሪ በነዳጅ ፍለጋ፣ ማልማት እና የማውጣት ሥራ፣ ልማቱ በሚካሄድበት አካባቢ በሚከናወን የነዳጅ ማጓጓዝና ማከማቸት ተግባር እንዲሁም ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘው ለወታደራዊ አገልግሎት በሚውል የነዳጅ አቅርቦት ሥራ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይገልፃል፡፡

**ክፍል ሁለት**

ስለ ግብይት ተዋናዮች ግዴታ የሚገልጹ ድንጋጌዎችን ይዟል፡፡ በአንቀጽ 4_የነዳጅ ውጤቶች አስመጪ ግዴታ የተዘረዘረ ሲሆን የሀገሪቱን የነዳጅ ፍላጎት መሠረት በማድረግ በየዓመቱ የግዥ ዕቅድ የማዘጋጀት፣ የጥራት ደረጃቸውን በማረጋገጥ ከውጪ አገር የነዳጅ ዉጤቶችን የማስመጣት፣ የማከማቸት እና ለነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች የመሸጥ ግዴታ እንዳለበት ይዘረዝራል፡፡

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት እንደማንኛውም ነዳጅ አስመጪ ድርጅት ተመሳሳይ ግዴታዎች ቢኖሩትም የመጠባበቂያ ነዳጅ የመያዝ፣ ችግር ሲያጋጥም ከመጠባበቂያ ክምችት ወጪ በማድረግ የማሰራጨትና ይህንኑ መልሶ የመተካት የተለዩ ሀገራዊ ግዴታዎች ያሉት በመሆኑ በአንቀጽ 5 ላይ ተጨማሪው የድርጅቱ ግዴታ በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡:

የነዳጅ ውጤቶች አከፋፋይ ግዴታ በአንቀጽ 6  የተመለከተ ሲሆን በሥሩ ቢያንስ አምስት መቶ ሺ ሊትር የነዳጅ ውጤቶች በክምችት መያዝ የሚችል ዴፖ እና አስር ማደያዎች የመገንባት፣ ከነዳጅ አስመጪ የተፈቀደለትን የነዳጅ ውጤቶች የመረከብ፣ የነዳጅ ውጤቶችን ለነዳጅ ማደያዎች እንዲሁም በባለሥልጣኑ ፈቃድ ለተሰጣቸው ቀጥታ ተጠቃሚዎች የማከፋፈል ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

በአንቀጽ 7 የተቀመጠው የነዳጅ ማደያዎች ግዴታ የነዳጅ ውጤቶችን ውል ከገቡበት አከፋፋይ ብቻ በመግዛትና በመረከብ ነዳጅ ማደያው ውስጥ እንዲራገፍ የማድረግ፣ ስለተራገፈው ነዳጅ ተገቢውን ማረጋገጫ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋው የኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ዘዴ ለነዳጅ አከፋፋዩ፣ ለነዳጅ አጓጓዡ እና ለባለስልጣኑ ወይም አግባብ ላለው አካል የመግለፅ፣ በማደያው

የተራገፈውን ነዳጅ በችርቻሮ ለነዳጅ ተጠቃሚዎች የመሸጥና ያልተቆራረጠ የሃያ አራት ሰዓት የሽያጭ አገልግሎት የመስጠት መሆኑ ተመልክቷል፡፡

የነዳጅ አጓጓዥ ግዴታ በአንቀጽ 8 የተዘረዘረ ሲሆን የነዳጅ ማጓጓዣውን የማስመርመርና ህጋዊ የካሊብሬሽን የምስክር ወረቀት የመያዝ፣ ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያው ጋር በገባው ውል መሠረት የጫነውን ነዳጅ በትዕዛዙ መሠረት የማጓጓዝ እና የማስረከብ፣ ከነዳጅ በስተቀር ሌሎች ማናቸውንም ጭነቶች በነዳጅ ማጓጓዣው ያለማጓጓዝ እና ከነዳጅ አስመጪ የጭነት ሰነድ በመያዝ ነዳጁን እንዲያጓጉዝ በተፈቀደለት መስመር ብቻ የማጓጓዝ፣ በተመደበለት መዳረሻ የማራገፍ እና በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም ሰነዱን የማሳየት ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

ሌላው ቀጥታ ተጠቃሚ በመባል የሚጠቀሱት ነዳጅን በቀጥታ ከአከፋፋይ በከፍተኛ መጠን የሚገዙ ትላልቅ ፕሮጀክቶችንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን የሚመለከተው አንቀጽ 9 ሲሆን የቀጥታ ተጠቃሚ ለመሆን ጥያቄያቸውን ለባለሥልጣኑ አቅርበው ፈቃድ የማግኘት፣ ከነዳጅ አከፋፋይ ኩባንያዎች የተረከቡትን የነዳጅ ውጤቶች አጠቃቀም ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ወይም በሚዘረጋ የኤሌክትሮኒክ የአሠራር ሥርዓት መሠረት የማሳወቅና የነዳጅ ውጤቶችን ከተረከቡበት ዓላማ ውጪ ያለመጠቀም ግዴታ እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡

**ክፍል ሶስት**

ስለ ተቆጣጣሪ አካላት፣ ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ስለ ግንባታ ፈቃድ የሚደነግግ ነው፡፡ በአንቀጽ 10 እና 11 ላይ እንደቅደም ተከተላቸው የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን እና የክልል ንግድ ቢሮዎች የመቆጣጠር ሥልጣን ተደንግጓል፡፡ በዚህ ረገድ የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር የማስተባበር፣ የመከታተልና የመቆጣጠር እንዲሁም ህጉ ተጥሶ ሲገኝ አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ መሆኑ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ አግባብ ያለው አካል በሚል ትርጓሜ የተሰጠው በክልል ንግድን_ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ደግሞ በክልሉ የቁጥጥር ሥራዉን በኃላፊነት በማገዝ ህገ-ወጥ የነዳጅ ዉጤት ግብይትን በመቆጣጠር አስተዋፅኦ ለማበርከት የሚያስችል ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

ከአንቀጽ 12 እስከ 15 ባሉት ድንጋጌዎች ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፣ ጸንቶ ስለሚቆይበት፣ ስለሚታደስበት፣ ስለሚታገድበት፣ ስለሚሰረዝበት እናለሌላ ሰው ስለሚተላለፍበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

በተከታዮቹ አንቀጽ 16 እና 17 ደግሞ ስለግንባታ ፈቃድ አሰጣጥና የግንባታ ፈቃድ ስለሚታገድበትና ስለሚሰረዝበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

**ክፍል አራት**

**ከአንቀጽ 18 እስከ 28** ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ ክፍል አንቀጽ 18 ላይ ስለ ዲጂታል የግብይት አሠራር የተደነገገ ሲሆን በዚህ ረገድ ማንኛዉም የግብይት ተዋናይ የነዳጅ ውጤቶች ግብይት ክፍያዉን በባለሥልጣኑ ዕውቅና በተሰጠው የዲጂታል የክፍያ ሥርዓት መፈፀም እንዳለበት እና ባለሥልጣኑ በየጊዜው የሚዘረጋውን እና በህዝብ ማስታወቂያ የሚያሳውቀውን ዲጂታል የግብይት ሥርዓት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡

ማደያ በሌለባቸዉ አካባቢዎች የሚፈጸም የነዳጅ ግብይትን በተመለከተ ደግሞ በመመሪያ እንደሚወሰን በአንቀጽ 19 ላይ ተደንግጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከአንቀጽ 20 እስከ 22 ስለሕገወጥ ነዳጅ ጠቋሚዎች፣ በግብይት ተዋናዮች ላይ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን በማገድ፣ በመሰረዝ ወይም ድርጅቱን በማሸግ ስለሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃና ስለቅሬታ አቀራረብ ተደንግጓል፡፡

አንቀጽ 23 ሕገወጥ ድርጊት ፈጽመው በተገኙ የግብይት ተዋናዮች ላይ የሚጣለውን የገንዘብና የእስራት ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን የወንጀል ቅጣት ድንጋጌ ማካተት ያስፈለገው በዘርፉ ከሚፈጸመው የሕግ ጥሰት ዐይነትና ክብደት ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ቅጣቶች በወንጀል ሕጉ ባለመካተታቸው እና ከሕገወጥ ድርጊቱ የሚገኘውን ትርፍ በማስላት የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ለመከላከል ነው፡፡

በመጨረሻም ከአንቀጽ 24 እስከ 28 የመተባበር ግዴታ፣ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ፣ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣ የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎችና አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ የሚሉ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

በአጠቃላይ ረቂቅ አዋጁ የነዳጅ ዉጤቶች አቅርቦት፣ ስርጭትና ግብይት ዘርፍን በተሟላ አግባብና ውጤታማ በሆነ አኳኋን ለማስተዳደር የሚያስችል እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ በረቂቁ ላይ በዘርፉ ከተሰማሩ የነዳጅ አከፋፋይ ድርጅቶች፣ ከነዳጅ ማደያ ባለቤቶችና የሥራ ሓላፊዎች እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተደጋጋሚ ውይይት የተደረገበት ሲሆን በውይይቱ

ወቅት ከተነሱት አስተያየቶች መካከል ማንኛውም የነዳጅ ውጤት አከፋፋይ  አምስት መቶ ሺህ ሊትር ነዳጅ የሚይዝ ዴፖ እና አስር ማደያዎች የመገንባት ግዴታ እንዳለበት የተደነገገው በነዳጅ አከፋፋዮች ከባድ ጫና ስለሚያስከትል በአግባቡ እንዲጤን የሰጡት አስተያየት በዋናነት ይጠቀሳል፡፡ በሕጉ አርቃቂ ተቋማት በኩል ደግሞ የነዳጅ ማከፋፈል ሥራ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅና ለሀገር ኢኮኖሚና ደህንነትም ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ አቅም ያላቸው አልሚዎች ብቻ ሊሰማሩበት እንደሚገባ ታምኖበት በዚሁ አግባብ ምላሽ ተሰጥቶበታል፡፡

ስለሆነም ረቂቅ አዋጁ በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላት፣ በዘርፉ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችና በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አካላት የሰጡትን ግብአት በማካተት በፍትሕ ሚኒስቴር ከሕግ አኳያ ታይቶ በተሰጡ አስተያየቶች እንዲዳብር የተደረገ በመሆኑ የተከበረው ምክር ቤት የረቂቅ አዋጁን አስፈላጊነት ተገንዝቦ እንዲያጸድቅልን በአክብሮት አቅርበናል፡፡